# ሰንደቅ ዓላማየን በጎሣ በጣጥሰው

በሽታ ሳይኖረኝ

ኮሶውን ግተውኝ፣

አረ ምን ይብጀኝ፤

አንጀቴን አመመኝ።

ጥሪ ሥጋን መብላት ኃጢያት ነው ብለውኝ፤

ኮሶው የጋጠውን ሆዴን ለማለሥለስ፣

ጥሬ ወትት እንኳን አንድ ጉንጭ እንዳልቀምስ፣

እሴት ነሽ በማለት ምለው አስገዝተው፣

ወተት ብቻ ሳይሆን መቀምጫም ነሱኝ።

# ሰንደቅ ዓላማየን በጎሣ በጣጥሰው፣

አሁንማ ጭራሽ ጋራ ሸንተረሩን

በገንዘብ ቸርችረው፣

እንኳን ዜግነቴን ሰው መሆኔን ነፍገው፤

አትኖሪም አሉኝ በኢትዮጵያ ምደር

እግዚር በፈጠረው።

ወይ ደፍረት፣ ወይ ድፍረት፤

ሰው ምሆኔ ቀርቶ ተተመንሁኝ በሐፍት።

ከሃምሣ ዓመታት በፊት፣

ኢትዮጵያን የማውቃት፤

በህዝቦቿ እንጅ፣ አልነበረም በሐፍት፣

ሐሰቱም እንደሆን ይመስክር ወልቃያት።

“በድርቅ የደቀቀው ህዝባችን፥ በአሁኑ ወቅት

ደግሞ በግጭቶች ሳብያ እያለቀ ነው።

ሃገር ከባድ ቀውጥ ውስጥ ገብታለች።

በእርስበርስ ግጭቶች…

ከድንበሩ ጀምሮ ማህሉ ድረስ ባለው

ህዝባችን ላይ የሞትና የመቁሰል ኣደጋዎች እየደረሱ ናቸው።…”

“በአረጋዊ በርሀ”

ጥቅሥ ከ [http://www.ethiomedia.com/1000bits/tiwlid-fetagne-kewt.pdf](http://www.ethiomedia.com/1000bits/tiwlid-fetagne-kewt.pdf)

አረጋዊ በርሄን እስኪ ጠይቁልኝ፤

ኢትዮጵያ እንዲህ እንድትሆን

ማን ጀመረው አሉኝ?

ምነው ገደላንስ እንዲህ የገለጹት፣

“ዓ/ም/ፈ የየአካባቢ ግጭት የሞተ ሰው ብዛት፣

2001 [እስከ]2011”

ምን ሊነግሩን ይሆን እንዲህ የጠቀሱት፤

ፍርድ ለማምጣት ይሆን
በኢትዮጵያ መሬት?
ምነው አቋረጡስ ከ2011 ወዲህ እንደዘረዘሩት
የሞተውን መቁጠር፤
በጎጃም፣ በጎንደር፣ በሌሎችም ጭምር።
አረጋዊ በርሄን እስኪ ጠይቁልኝ፤
ኢትዮጵያ እንዲህ እንድትሆን
ማን ጀመረው አሉኝ?

**ሰንደቅ ዓላማየን በጎሣ በጣጥሰው**

እንኳን ዜግነቴን ሰው መሆኔን ነፍገው፤
አትኖሪም አሉኝ በኢትዮጵያ ምድር
እግዜር በፈጠረው።

© ለምለም ፀጋው ፣ September 24, 2017

“ትውልድ ፈታኝ ቀውጥ!!! (አረጋዊ በርሀ)” ጽሑፍ የተጸነሰ

ከ http://www.ethiomedia.com/1000bits/tiwlid-fetagne-kewt.pdf የተገኘ